# ጥገናዎች

## ተከራዮች: መብቶችዎን ይወቁ!

**ከሚከተሉት ሁኔታዎች በስተቀር አከራይዎ ጥገናን በመጠየቅ ሊያስወጣዎ አይችልም:**

| | | |
|---|---|---|
| እርስዎ ወይም የእርስዎ እንግዶች ምክንያታዊ ባልሆነ መንገድ በመንቀሳቀስ ጥገና የሚያስፈልገው ችግር ከፈጠሩ | የቤት ኪራይ ክፍያ ካልከፈሉ | ችግሩን ለማስተካከል እርስዎ እንዲለቁ የሚያስገድድ ከፍተኛ የጥገና ስራ ካለ |

**ባለንብረቱ እርስዎን ለማስወጣት ከሞከረ፣ የማስለቀቂያ ባለመብቶች ጋር በመደወል ያማክሩ።**

### አከራዮ ለእነዚህ ነገሮች ኃላፊነት አለበት...

- ቦታውን ለኑሮ ምቹ አድርጎ ማቆየትና በጥሩ ሁኔታ መጠገን።
- ሁሉም ሰው የሚጠቀምባቸውን ቦታዎች ንፁህ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ማድረግ።
- የጥገናው ጥያቄ ከቀረበ በኋላ በኪራይ ውሉ ላይ በተጠቀሰው መሠረት ተመጣጣኝ በሆነ ጊዜ ውስጥ ጥገናውን ማድረግ

**የኪራይ ውልዎ እንዲህ የሚል ከሆነ፣ እራስዎ አንዳንድ ጥገናዎችን ማድረግ ሊኖርብዎት ይችላል።**

### ጥገናዎችን እንዴት መጠየቅ እችላለሁ?

**ሁልጊዜም የጥገና ጥያቄዎን በጽሁፍ** ማቅረብ አለቦት። ጥያቄውን ያቀረቡበትን **ቀን** እና ባለንብረቱ እንዲያስተካከል የሚጠይቁትን **ጉዳይ** የሚያካትት ደብዳቤ፣ ኢሜል ወይም የጽሑፍ መልእክት ለአከራይዎ ይላኩ። ጥያቄውን ስለማቅረብዎ ማረጋገጫ እንዲኖርዎ **የኮፒ ቅጂ** አዘጋጅተው ያስቀምጡ።

**ባለንብረቱ ጥገናውን በምክንያታዊ ጊዜ ውስጥ ካላደረገ የኪራይ ውልዎን ቀደም ብለው ጨርሰው መውጣት ይችላሉ። በቅድሚያ የማስለቀቂያ ባለመብቶች ጋር በመደወል ምክር ያግኙ።**

### ድንገተኛ ችግር ከሆነስ?

እንደ **መብራት፣ ሙቀት መቆጣጠሪያ፣ ጋዝ፣ ውሃ፣ ፍሳሽ ወይም ቧንቧ** አይነት አስፈላጊ የሆነ ነገር ቢሰበርብዎት እና ለባለንብረቱ የጽሁፍ ጥያቄ ካቀረቡ በኋላ ወዲያውኑ ካልተስተካከለልዎ በህግ የተፈቀዱ **ልዩ መብቶች እና አማራጮች** አልዎት።

የህግ ባለሙያም ሊረዳዎ ይችላል:

- **ነገሮችን ለማስተካከል የተወሰነውን የኪራይ ገንዘብ ይጠቀሙ።**
- **ባለንብረቱን ይክሰሱ።**
- ጥገናውን በሚጠባበቁበት ወቅት **የኪራይ ገንዘብዎን በሌላ በሚቆዩበት ቦታ ይጠቀሙ።**

**ባለንብረቱ ጥገና አላደረገም ብለው የቤት ኪራይ መክፈልዎን አያቁሙ።**

**የቤት ኪራይ አለመክፈል አብዛኛውን ጊዜ የኪራይ ውልዎን ያፈርሳል።** ይህ ከሆነ፣ **ባለንብረቱ ሊያስወጣዎት ይችላል።** ባለንብረቱ ማስተካከል ያለበትን ነገር ለማስተካከል **የራስዎን ገንዘብ** አውጥተው ከሆነ **ዳኛው ገንዘቡ እንዲመለስልዎት** ማድረግ ይችላል። ምን ያህል እንዳወጡ ለማሳየት **ደረሰኞችዎን ያስቀምጡ።**

ቤትዎ እንደ ደካማ **የኤሌትሪክና ቧንቧ ዝርጋታ ወይም የበሰበሰ እንጨት** ባሉ ችግሮች ምክንያት **ደህንነቱ ያልተጠበቀ** ከሆነ፣ ለሜትሮ ኮድ አስተዳደር በ (615) 862-6590 መደወል ይችላሉ። እንደ **ቆሻሻ፣ ነፍሳት ወይም አይጥ** ባሉ ችግሮች ምክንያት **ጤናማ ያልሆነ** ሁኔታ ከተፈጠረ፣ ለሜትሮ ጤና ጥበቃ ክፍል በ (615) 340-5616 መደወል ይችላሉ።

**REPAIRS**

LEGAL AID SOCIETY OF MIDDLE TENNESSEE AND THE CUMBERLANDS (833) 837-የቤት

AMAC American Muslim Advisory Council (615) 988-6460

conexión américas (615) 701-7957

Nashville Hispanic Bar Association

**ለዴቪድሰን ክልል ብቻ።** እዚህ የቀረበው መረጃ የህግ ምክርን አይመሰርትም፤ ለመመስረት የታሰበም አይደለም። የሕግ ችግር ካጋጠመዎት፣ እባክዎን ለግል ጠበቃዎት ይደውሉ ወይም በአካባቢዎ የሚገኘውን የመካከለኛው ቴነሲ የሕግ ድጋፍ ማህበር እና የኩምበርላንድ ቢሮ በ1-800-238-1443 ወይም የናሽቪል የሂስፓኒክ ባር ማህበርን በ1-615-701-7957 ይደውሉ።

በ5/23 ተሻሽሏል።